

## የቆሎው ተማሪ ።

ምናልባት ዕድሜና ጤናው ቢገኝ ከዚህ በተሻለ ይዘታ እንደገና ክልሼውን በደንብ አሠርቼ ለማሳተም ተስፋ አለኝ፤ ይሁን እንጅ ፈቃዱ የእግዚአብሔር ነው ።

«እስመ ዘእንበሌየሰ ኢትክሉ ገቢረ ምንተኒ» ያለኔ ፈቃድ ምንም ምን ልታደርጉ አትችሉምና፤ ብሏል፤ ዮሐ ም ፲፭ ቍ ፭።

# ·ዊው የቆሎ ተማሪ ።



የዛሬን ለነገ ካላኖሩት ጽፈው
ከዋለ ካደረ አርኬዎሎጂ ነው ።

አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

R/4003/76

# ጥንታዊው የቆሎ ተማሪ ፡፡

ቅድስት ሥላሴ ... ቤተ መጻሕፍት

የዛሬን ለነገ ካላኖሩት ጽፈው
ከዋለ ካደረ አርኬዎሎጂ ነው ።

ከአባ ኪዳነ ማርያም ጌታሁን
ተ ዘ ጋ ጀ ።

1587
እቴጌ ፡ መነን ፡ ት/ቤት ፡ ቤተ
EMPRESS MENEN SCHOOL
LIBRARY

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፳፪ኛው ዘመን መንግሥት
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቀዳማዊ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ በሆኑ በ፫ኛው ዓመት
ይህ መጽሐፍ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

ያለደራሲው ፈቃድ መልሶ ማሳተም
ክልክል ነው ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቀዳማዊ
የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ።

www.ethiopianorthodox.org

## የባለውለታዎቼ ሊቃውንት አጭር የሕይወት ታሪክ ፤

ይህን መጽሐፍ ባዘጋጀሁበት ጊዜ ስለጥንቱ ት| ቤት ባህልና ሥርዓት በአሳ በሥራ ለረዱኝ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከጭር የሕይወት ታሪካቸው ጋር ከፍ ምስጋናዬን ከዚህ እንደሚከተለው በትሕትና አቀርባለሁ ።



ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሐረር ጠ| ግዛት ሊቀ ጳጳስ ።

፩ኛ የሐረርጌ ጠ/ ግዛት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ወርቅ የሆነ የሥራ ...ዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው በማረምና በማስተካከል ስለደከሙልኝ በኔ አን ...በት የሚበቃ ምስጋና ላቀርብላቸው አልችልም ።

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሐዲስ፣ የፍትሐ ነገሥትና የቅኔ መምህር ናቸው ፤ ...ህም ሌላ የውጭ አገር ቋንቋ እንግሊዝኛና ጣሊያንኛ ያውቃሉ ፤ እርሳቸውም ... ትዕግሥትና እርቆ ተመልካችነት ፤ ማስተዋልም የባሕርይ

www.ethiopianorthodox.org

# መ ጀ መ ሪ ያ ክ ፍ ል ።

## ጥንታዊው ተማሪና የሐሳቡ ግብ ።

አንድ የዱሮ ተማሪ ከእናትና ከአባቱ ተለይቶ ለትምህርት ወደ ሩቅ አገር ለመሔድ በተነሣ ጊዜ ዋና አሳቡ ዜማና ቅኔ ተምሮ ሲመለስ በተወለደበት አገር ቤተ ክርስቲያን ፤ በዲቁናና በቅስና ወይም በመሪጌትነት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ፤ እራሱን እየረዳ ለመኖር ብቻ ነው ። የተማሪው ሐሳብ እንደዚህ ባጭሩ የተወሰነ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ወደፊት እየገፋፋው መጻሕፍተ ብሉያትንና መጻሕፍተ ሐዲሳትን ጠንቅቆ አውቆ በኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአንድ ገዳም መምህር ወይም እጨጌ ፤ ከዚህም ሌላ ከፍ ብሎ ጳጳስ ለመሆን የሚመረጥበት በቂ እውቀትና ሙሉ ግብረ ገብነት ያለው ሆኖ ይገኛል ።



ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ይገሠግሳል ።

ተማሪውም ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ሲዘጋጅ ለእናትና ለአባቱ አያማክራቸውም ፤ ምክንያቱም ፤ ኢትፈር ኀቤሃ ለጥበብ በ፪ዔ ልብ ፡ አላ ኩን ከመ ዘይዘርዕ ወየዓፅድ (መንፈሳዊና ሥጋዊ ፡ ጥበብን ለመማርና ለመመራመር በአሰብህ ጊዜ ሁለት ልብ ሆነህ አትሥማራ ፤ በአንድ ዓይነት ሐሳብ ሆኖ እንደሚዘራና እንደ ሚያ [illegible] ተባለውን የምናኔ ምክር ነባቢት ነፍሱ ስለምታውቀው

www.ethiopianorthodox.org

